# ዴሞክራሲ ከእውነተኛ ባለቤቱ እጅ ገብቷል

*አሜን ተፈሪ 06-13-18*

ያ ‹‹ፖለቲካዊ ጠሮ›› (Political Hurricane) ብዙ ካንገላታን በኋላ አሁን ደብ ብሏል፡፡ ነጠላ እንደሚቋጭ ሰው፤ አዕምሮዬ ሁለት ነገሮችን መቋጨት እና ማሰላሰል ይዟል፡፡ በሁለት ሐሳቦች ቅኝት ያንጎራጉራል፡፡ አንዱ የደስታ፤ ሌላው የመጓደል ቅኝት ነው፡፡ እኒህን ሁለት የህሊና ቅኝቶች ድምጽ እንዲያገኙ ለማድረግ እጽፋለሁ፡፡ በደስታ የማውጠነጥነው ነገር፤ የዴሞክራሲ ስርዓት ከእውነተኛ ባለቤቱ እጅ መግባቱን በመመልከት የተፈጠረውን ደስታ ነው፡፡ በመጓደል ስሜት የሚጎተጉተኝ ነገር፤ አሁንም በማንነት ላይ ያተኮረ ጥቃት ሲከሰት አልፎ አልፎ መስማቴ ነው፡፡

መንግስት የችግሩ ምንጮች የአመራር ጉድለት እና የመልካም አስተዳደር ችግር መሆኑን በተደጋጋሚ ያወሳል፡፡ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ሌሎች ነገሮችንም እንደ ምክንያት ያነሳል፡፡ ለችግሩ ምክንያት ሆነው የታዩትን ነገሮችም ለማሻሻል ጥረት እያደረገ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ ሊነሳ የሚችለው የሰላም ኮንፈረንሶች መካሄዳቸው ነው፡፡

ሆኖም በዚህ ጽሑፍ ማትኮር የምፈልገው ‹‹ዴሞክራሲ ስርዓቱ ከእውነተኛ ባለቤቷ እጅ ገባች›› በሚል በጠቀስኩት ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ረገድ የማነሳውን ነገር ለማቅረብ አንድ ምሣሌ እጠቀማለሁ፡፡ ይህ ምሣሌ ወደ ቻይና ይወስደኛል፡፡ ቻይና ሄጄ የማነሳው የአንድ ቻይናዊ ፈላስፋ ታሪክን ነው፡፡ ባለታሪካችን ‹‹ሳንዙ›› ይባላል፡፡ ሳንዙ፤ ክርስቶስ ከመወለዱ ከ500 ዓመታት በፊት በምድረ ቻይና የተመላለሰ ፈላስፋ ነው፡፡ የጦርነት ባለሙያ ነው፡፡ ሳንዙ በዓለም ህዝብ ዘንድ የሚታወቀው ‹‹የጦርነት ጥበብ›› (The Art of War) በተሰኘ መጽሐፉ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ የተጻፈው፤ ወደ ጎን 25 የሚደርሱ የቻይና ፊደላትን መያዝ በሚችሉ እና ማስመሪያ በመሳሰሉ ቀጫጭን የሸንበቆ ቁርጥራጮች ላይ ነው፡፡ ሳንዙ፤ በጥንታዊት ቻይና ‹‹ሁ›› የተባለች ግዛት የተወለደ ሲሆን፤ የሐገሩ ንጉሥ ‹‹ሐሉ›› ይሰኛል፡፡

ንጉስ ‹‹ሐሉ›› ክፉ ጎረቤት ነበረው፡፡ ‹‹ው›› በተባለች ግዛት የነገሠው፤ የንጉሥ ‹‹ሐሉ›› ክፉ ጎረቤት፤ ክፉ አሰቦ ዝግጅት ጀመረ፡፡ ወታደራዊ አቋሙን ማጠናከር ያዘ፡፡ ታዲያ ይህን ሁኔታ የተመለከተው ንጉሥ ‹‹ሐሉ›› ራሱን ማዘጋጀት እንዳለበት አሰበ፡፡ ስለዚህ የጦር ባለሙያ ያልነውን ‹‹ሳንዙ››ን ጠርቶ ምክር ጠየቀው፡፡ ‹‹ሳንዙ›› የጦር መሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ነጋዴዎች እና ሌሎች ሰዎች

ጭምር መመሪያ አድርገው የሚጠቀሙበትን ዘመን ተሻጋሪ ጥበብ ያስተማረ ፈላስፋ ነው፡፡ በዚህ የጦር ባለሙያ እምነት ‹‹የተደራጀ እና ብቃት ያለው ሠራዊት እንጂ የጀሌ መብዛት ፋይዳ የለውም፡፡››

ስለዚህ በርካታ ሠራዊት ካለው እና ለወረራ ዝግጅት ሲያደርግ ከነበረው የ‹‹ው›› ንጉሥ የሚሰነዘርን ጥቃት በብቃት ለመመከት፣ ብቃት ያለው እንጂ ብዛት ያለው ሠራዊት አያስፈልግም የሚል እምነት የነበረው ‹‹ሳንዙ››፣ ‹‹ማንኛውንም ሰው ምርጥ ወታደር ማድረግ ይቻላል›› ብሎ ያስብ ነበር፡፡ ስለዚህ ንጉሡ፣ ‹‹አንተ ማንኛውንም ሰው ብቁ ወታደር ማድረግ ይቻላል ትለኛለህ፡፡ እንዲያው ለመሆኑ፣ እነዚህን የቅልጣን ኑሮ የለመዱ፣ በዶሮ ላባ ሊደማ የሚችል የላመ ሰውነት ያላቸውን ሞልቃቃ የጭንገረዶች ብቁ ወታደር ልታደርጋቸው ትችላለህን?›› ሲል ‹‹ሳንዙ›› ጠየቀው፡፡

‹‹ሳንዙ›› ለንጉሡ ጥያቄ የሰጠው መልስ ‹‹ያለ አንዳች ጥርጥር ብቁ ወታደር ላደርጋቸው እችላለሁ›› የሚል ነበር፡፡ እናም የንጉሡን የጭንገረዶች ማሰልጠን ጀመረ፡፡ የጭንገረዶቹን ሰብስቦ ራስን የመከላከል ወታደራዊ ጥበብ ለማስተማር ሲሞክር፣ እኒያ ከቅምጥል ህይወት በቀር ሌላ የማያውቁ ሴቶች ተቸገሩ፡፡ ‹‹ሳንዙ››ም ግራ ተጋባ፡፡ ሆድ የሚያንቀጠቅጠው ከበሮ ቢደለቅ ቢነረትም ሴቶቹ ‹‹ሳንዙ›› የሚያሳያቸውን አካላዊ እንቅስቃሴ ተከትለው መንቀሳቀሱን ትተው ማሽካካት ያዙ፡፡ አስቸገሩ፡፡

‹‹ሳንዙ›› ከሚጠቅሳቸው መርሆዎች አንዱ፣ ‹‹ትዕዛዝን ግልጽ ባለማድረግ የሚፈጸም ስህተት የጄነራል፣ ትዕዛዙ ግልጽ ሆኖ ሳለ የሚፈጸም ጥፋት የሠራዊት ነው›› የሚለው አንዱ ነው፡፡ ስለዚህ ‹‹ሳንዙ›› ለጭንገረዶቹ የሰጣቸው ትዕዛዝ ግልጽ መሆኑን አረጋግጦ፣ የጀመረው ሥራ ቧልት ወይም ጨዋታ አለመሆኑን ለማስረዳት ጥረት ቢያደርግም ሴቶቹ እየቧለቱ እና እየተሽኮረመሙ አስቸገሩ፡፡ በዚህ ጊዜ የጭንገረዶቹ ‹‹ጠርናፊ›› የሆኑ ሁለት ሴቶች፣ ከቆሙበት ሰልፍ አንድ እርምጃ ወደፊት እንዲወጡ አዘዘ፡፡ እርሱም ከሁለቱ ሴቶች መሐል ገብቶ፣ ሰልፍ አሳምሮ ከቆመ በኋላ ሰይፉን ከሰገባው መዝዞ ግራ ቀኝ በመሰንዘር የሴቶቹን አንገት እየቀላ ከሰልፈኞቹ ፊት ጣለው፡፡ ያሳዝናል፡፡ ግን ከዚያች ቅጽበት ወዲያ ሴቶቹ ወታደር ሆኑ፡፡ እናም የሚሰጣቸውን ተልዕኮ እና ግዳጅ ለመፈጸም የሚያስችል ብቃት አገኙ፡፡

ይህ ታሪክ የተጠቀሰው ምሣሌ ሆኖ እንዲያገለግል ነው፡፡ እናም በምሣሌው፣ ‹‹ሳንዙ›› ህዝብ ነው፡፡ የሳንዙ ትዕዛዝ፣ የህዝብ ትዕዛት ነው፡፡ የሳንዙ ቁጣ፣ የህዝብ ቁጣ ነው፡፡ የህዝብ ቁጣ በሩቅ የሚያስፈራ የተባ ሰይፍ ነው፡፡ ‹‹ግርማው›› ብቻ ያስፈራል፡፡ ባለፉት ሁለት እና በያዝነው ዓመት መጀመሪያ

በሐገራችን ያየነው ‹‹ፖለቲካዊ ጠሮ›› (Political Hurricane)፣ አስፈሪ የህዝብ ቁጣ፣ ከሰይፍ የሚቆጠር ነው፡፡ ይህ ቁጣ በገዢው ፓርቲ አመራሮች ዘንድ የሚታዩትን ችግሮች ለማስተካከል አስገዳጅ ሁኔታ የፈጠረ ነበር፡፡ የህዝቡ ጥያቄ ፈጽሞ ቸል ሊባል የማይችል ህዝባዊ ግፊት ፈጠረ፡፡ ፓርቲው በጥልቀት የመታደስ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲገባ አደረገ፡፡ ታዛዡ አዛዥ የሆነበት ሁኔታ እንዲቀየር አደረገ፡፡

እንዲህ መሆኑ ለበጎ ነው፡፡ አሁን የተፈጠረው የለውጥ እንቅስቃሴ ከገዢው ፓርቲ መልካም ፈቃድ የመነጨ ከሚሆን፣ እንዳሁኑ በህዝብ ግፊት የተቀሰቀሰ መሆኑ ለዴሞክራሲ ስርዓቱ መጠናከር አወንታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡ ይህ ሂደት እንደኛ ላለ የዴሞክራሲ ስርዓት ጀማሪ ለሆነ ህዝብ የሚሰጠው ትልቅ ትምህርት አለ፡፡ በርግጥ የመንግስት ባህርይ፣ አሰራር እና አደረጃጀት በህዝብ ፈቃድ የሚወሰን መሆኑን ለማየት ቻልን፡፡ ህዝቡ የተሰጠውን ነገር እየተቀበለ የሚኖር ግዑዝ ፍጡር ሳይሆን፣ በነጻ ምርጫው ሥልጣን የሰጣቸው መሪዎቹ እርሱ የሚፈልገውን ከማድረግ ውጭ ሌላ አማራጭ እንደሌላቸው እንዲያውቁ አደረገ፡፡ መሪዎች የህዝብን ፈቃድ ለመፈጸም የማያቅማሙ አመራሮች እንዲሆኑ አደረገ፡፡ ይህ ሂደት ለዴሞክራሲ ስርዓታችን እሴት የሚጨምር ይመስለኛል፡፡

ህዝቡ በመሪዎች ችሮታ በተሰጠው በጎ ነገር የሚጠቀም እና በመሪዎቹ ንፍገት የሚበደል ህዝብ ሳይሆን፣ የሚገባውን ነገር ማንም በችሮታ መልክ ሊሰጠው ወይም በንፉግነት ሊከለክለው የማይችል ሉዓላዊ የሥልጣን ባለቤት መሆኑን በግልጽ አረጋገጠ፡፡ ይህ ለሐገራችን የዴሞክራሲ ስርዓት እሴት የሚጨምር ክንውን ነው፡፡ በሌላ በኩል፣ ህዝቡ መብቱን ለማስከበር የሚያደርገው ጥረት በህግ የተባረከ፣ በዴሞክራሲያዊ እሴቶች የታነጸ እንዲሆን ማድረጉ የሚበጀው መሆኑን ለመረዳት ልዩ ዕድል የፈጠረለትም ይመስለኛል፡፡ ከህግ የወጣ ነገር ለህገ ወጦች ፍላጎት ሲሳይ ሊያደርገው፣ መብቱን እና ነጻነቱን ለመሸርሸር የሚያመች ሁኔታን ሊጎትትበት እንደሚችል ለመገንዘብ የሚያስችል ተግባራዊ ትምህርት መቅሰም አስችሎታል የሚል እምነት አለኝ፡፡

ፖለቲካዊ ምህዳሩን በአስፈሪ አውሎ ነፋስ ሲተራምሰው የነበረው ‹‹ሃሪኬን›› አልፎ ምድረ-ፖለቲካው ደብ ብሏል፡፡ በርግጥ የገጠመን ፈተና ቀላል አልነበረም፡፡ አንድን ሐገር እንደ ሐገር የሚያቆሙ ህብረተሰባዊ መዋቅሮቻችን ሁሉ በአስደንጋጭ ሁኔታ ተርገድግደው ነበር፡፡ በበኩሌ፣ ሐገሬ በዚህ መጠን ስትቸገር በዓይን ያየሁበት ሌላ የታሪክ አጋጣሚ የለም ለማለት የሚያስደፍረኝ ነው፡፡

ታዲያ በተፈጠረው ሁከት ጥቃት የደረሰበት ዘመናትን ያስቆጠረው የህዝባችን የአብሮ መኖር ባህል ጭምር ነው፡፡ በዚህ ነባር የህዝቡ ባህል ላይ የደረሰው ጥቃት ከፍተኛ ድንጋጤ የፈጠረ እና ከባድ የሐዘን ስሜት አሳድሮ ያለፈ ነበር፡፡ በአብሮ መኖር የሰለጠነ አስተሳሰብ ወይም ባህላዊ ደመ-ነፍስ ያዳበረው ህዝባችን በከባድ ሁኔታ ተፈትኗል፡፡ ይህ የህዝባችን ዘመን ተሻጋሪ ቅርስ በስሜት እሣት እና በሐኬተኛ ፖለቲከኞች ጉዳት ደርሶበታል፡፡ በበኩሌ፣ ሐገር ሊሞት ሲል ምን ዓይነት የበሽታ ምልክቶች እንደሚታይበት ለመረዳት አስችሎኛል፡፡ የመረጃ ዘመን ቴክኖሎጂ በረከት እና መርገም በውል ታይቶኛል፡፡ የመረጃ ዘመን ቴክኖሎጂ ለሐገር ኸረት የሚጠቅመውን ያህል፣ የሐገርን ሞት ለመጎተት ወይም ለማፋጠን ትልቅ ሚና ሊጫወት እንደሚችል አሳይቶኛል፡፡

በረጅም ዘመን ሂደት የተገመደው እና ለብዙዎች እንደ ትንግርት የሚታየው የህዝባችን ጥብቅ ማህበራዊ ትስስር እና የአብሮ-ተከባብሮ መኖር ባህል፣ ምን ዓይነት ፈታናዎች እንደተጋረጡበት ለመረዳት የሚያግዝ ክስተት አድርገን ለማየት እንችላለን፡፡ ከሦስት ወይም ከአራት ዓመታት በፊት በመዲናችን በተካሄደ አንድ ጉባዔ ተሳታፊ እና ንግግር አቅራቢ የሆኑ አንድ የውጭ ሐገር ሰው (ምናልባት ሙስሊም - አረባዊ) በአፍሪካ ህብረት አዳራሽ ባደረጉት ንግግር፣ ‹‹ኢትዮጵያውያን ድንቅ የአብሮ መኖር እና የመቻቻል ባህል አጽንታችሁ ቆይታችኋል፡፡ ዛሬ ይህን አኩሪ ቅርሳችሁን ይዛችሁ መቀጠል መቻል - አለመቻላችሁ ከሚፈተንበት ዘመን ደርሳችኋል፡፡ ኢትዮጵያውያን የሐይማኖት ልዩነት ችግር ሳይፈጥርባችሁ በአንድነት ለመኖር መቻላችሁ ያስደንቃል፡፡ ይህም በብዙ ቦታ ሊገኝ የማይችል ልዩ ቅርሳችሁ ነው፡፡ ሆኖም 21ኛው ክፍለ ዘመን ያመጣውን ፈተና ተቋቁሞ ለማለፍ እና ዓለም የሚደነቅበትን አኩሪ የአብሮ መኖር እሴት በመጠበቅ መጓዝ መቻላችሁ የሚታየው በወደፊቱ አካሄዳችሁ ይሆናል›› (ቀጥተኛ ጥቅስ አይደለም) በማለት ተናግረው ነበር፡፡ እኚህ ሰው በሐይማኖት እና በማንነት ሰበብ የሚፈጠሩ ግጭቶች ከመንገድ እንዳያወጡን እና ነባር ቅርሳችንን እንደ እሣት መድምደው እንዳያጠፉት በማያንቀላፋ ትኩረት መጠበቅ እንዳለብን አስታውሰውናል፡፡

ከዚህ አንጻር ባለፉት ዓመታት እና በያዝነው ዓመት መግቢያ አካባቢ በታየው ‹‹ፖለቲካዊ ሃሪኬን›› ሳቢያ የተፈጠሩ የመጠራጠር ስሜቶችን ማከም እና አሁን ብልጭ ድርግም የሚሉ ግጭቶችን ያለንን አቅም ሁሉ በማስተባበር መፍታት ይኖርብናል፡፡ ይህን የመቃቃር እና የመጎዳት ስሜት በጥናት ላይ ተመስርተን፣ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ባረጋገጠ አግባብ ቁስሉ እንዲሽር ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ችግሩን ከሚገባው በላይ አጋንኜ ለማየት አልፈልግም፡፡ የህዝብን አብሮ የመኖር ባህል

የሚነዱ ችግሮች የተፈጠሩት በጥቂቶች መሆኑን አምናለሁ፡፡ ድርጊቱ የህዝብን ስሜት አያንጸባርቅም፡፡ ለዚህም ነው ችግሩ ድንገት ቦግ ብሎ ወዲያው ሊከስም የቻለው፡፡ ይሁንና ችግሩ በጊዜው በብዙዎች ዘንድ የመጠራጠር፣ የድንጋጤ፣ ግራ የመጋባት እና የጭንቀት ስሜት መፍጠር የቻለ፤ ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ (ለሥራ ሆነ ለትምህርት) ለመሄድ የማመንታት ሐሳብ ያሳደረ ችግር ሆኖ አልፏል፡፡

በመሆኑም፤ አሁን የችግሩ ፖለቲካዊ አደጋ የታገሰ መሆኑ ቢታይም፤ ፈጥሮት የነበረው ስሜት መልሶ ቢረጋጋም፤ በቀላል ችግር ሊያገረሽ የሚችል ህመም የመሆን ዕድል ያለው ይመስለኛል፡፡ ‹‹እባብ ያየ በልጥ በረየ›› እንዲሉ፤ ወደፊት ልጥ በታየ ቁጥር የመበርገግ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል በመገመት፤ የችግሩ ሰንኮፍ ከሥሩ ተነቅሎ እንዲወድቅ ማድረግ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ ስለዚህ የችግሩን ትክክለኛ ምንጭ እና የድርጊቱ ዋና ተዋናዮች በደንብ ተለይተው፤ ወደፊት ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ዝግጁ ሆኖ ለመገኘት የሚያግዝ የህሊና ልምድ መቀመር ያስፈልጋል፡፡ የተፈጠረው የሥነ ልቦና ቁስል እንዲሽር ማድረግ ይኖርብናል፡፡ ችግሩ በፖለቲካዊ ግምገማ ብቻ ተወስኖ መፍትሔ በመስጠት ሊቃለል የሚችል አይደለም፡፡

በሁከቱ የተቃጠሉ የግለሰብ ቤት እና ንብረቶችን እንዲሁም መንግስታዊ ተቋማትን በህብረተሰቡ ተሳትፎ መልሶ ለመገንባት ጥረት እንደሚደረግ ሁሉ፤ የታቃጠሉ የአብሮ መኖር ስሜታዊ እና መንፈሳዊ ጓዞችም በሰፊ የህዝብ ተሳትፎ መልሰው ሊገነቡ ይገባል፡፡ እንዲያውም የተቋማት መልሶ ግንባታው መነሻ መደረግ ያለበት የመንፈሳዊ እና ስሜታዊ ንብረቶችን መልሶ በመገንባት ሊሆን ይገባል፡፡

የቀውሱ ሙሉ አንድምታዎች መታየት፤ የአፈጣጠር ሂደቱ መመርመር፤ ችግሮቹን እነማን ለጥፋት ዓላማ ተጠቀሙባቸው የሚለውን በውል መንቀስ፤ የተከተላቸውን ጎዳናዎች ሁሉ መለየት፤ በአጠቃላይ የችግሩ መጋቢ የቀውስ ወንዞች እና ተፋሰሳቸው ጭምር በዝርዝር መጠናት ይኖርበታል፡፡ ችግሩን በደምሳሳው ማስቀመጥ ሳይሆን በዝርዝር ጥናት አብጠርጥሮ ማወቅ አስፈላጊ ይመስለኛል፡፡ በዚህ መንገድ ችግሩን ከተረዳነው፤ ወደፊት ተመሳሳይ ችግሮች ሲያጋጥሙን፤ ምን በምን አግባብ መከላከል እንደምንችል አውቀን፤ ሳንደነባበር ፈጣን ምላሽ መስጠት እንችላለን፡፡ ምናልባትም፤ ችግሩ እንዳይፈጠር ማድረግ እንችላለን፡፡ ችግሮች ከተፈጠሩም እግር አውጥተው ለመራመድ ከሚችሉበት ደረጃ ሳይደርሱ በእንጭጩ ለመቅጨት እንችላለን፡፡ ‹‹ሠይጣን›› የሚያድረው በዝርዝሮች ውስጥ ነው፡፡ ስለዚህ ሠይጣኑን ለማባረር ዝርዝሩ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

በተረፈ፤ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 88፣ ንዑስ አንቀጽ 2 እንዲህ ይላል፤ ‹‹መንግስት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችን፣ የህዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ መርህ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡›› የክልል መንግስታት ይህን ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት ለመወጣት በርትተው መስራት ይባቸዋል፡፡